# አገራዊ ምክክር ውጤታማ የሚሆነው አካታች ሲሆንና ሂደቱም ነፃና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ውሳኔዎቹን ለመተግበር አስቻይ ሁኔታዎች ሲኖሩ ነው!

## ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ኢሕአፓ የተሰጠ መግለጫ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአንድ ቀውስ ወደ ሌላ ቀውስ እየገባች፣ የጋራ እሴቶቻችን፣ ሀገራዊ ራዕያችንና ለዘመናት ሕዝባችን አጋምደው ያኖሩን ትስስሮቻችን እየተሸረሸሩ ሄደው ሊጠገኑ ወደማይችሉብት ደረጃ ላይ የተደረሰበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። በሕገ መንግሥቱ፣ በክልሎች አወቃቀር፣ በሀገረ መንግሥት ምሥረታ...ወዘተ ላይ ያለው አመለካከት ሰፊና ተፃራሪ ነው። በሀገራዊ ተቋሞቻችን፣ በሰንደቅ ዓላማና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የጋራ ዕይታችን እየተራራቀ ከመጣ ውሎ አድሯል።

ሀገራችንን እንደ ሀገር በማስቀጠል ላይ የአመለካከት ልዩነቶች ከመስተዋላቸው በተጨማሪ በጋራ ታሪካችን ላይም ሰፊ አለመግባባት ይታያል። ከሁለት ዓመታት በፊት በህወሓትና በብልጽግና መካከል የተቀሰቀሰው የፖለቲካ ቀውስ ወደ ከፍተኛ ድረጃ ደርሶ የአንድ ሚሊዮን ወገኖቻችንን ሕይወት ወደቀጠፈው ጦርነት እንደተሸጋገረ ይታወሳል። ጦርነቱ የብዙ ቢሊየን ብር የኤኮኖሚ ኪሳራም አድርሷል። ይህ አልበቃ ብሎ አገራችን ዛሬም በኦሮሚያ በቤኒሻንጉል፣ በአማራ፣ በጋምቤላ በሌሎችም አካባቢዎች በጦርነት ውስጥ ትገኛለች። ስለዚህ ከአውዳሚ የርስ-በርስ ጦርነት አዙሪት ውስጥ መውጣት ለኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ ሳይሆን የግድ በመሆኑ ይህን ሊያሳካ የሚችል ሀገራዊ ውይይት፣ ድርድርም ሆነ ምክክር ተደርጎ ብሄራዊ መግባባት መገኘቱ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ኢሕአፓ አጥብቆ ያምናል፡፡

ኢሕአፓ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተስፋፉ የመጡትን ቀውሶች በአገራዊ በቅንነት ምናልባት በድርድርና ምክክር ሊፈቱ ይችሉ ይሆናል በሚል ተስፋ ለተወሰኑ ዐመቶች ሲሳተፍባቸው ቆይቷል። ይሁን እንጂ ገዥዎቻችን ችግሮችን በቅንነትና በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ አገራዊ ምክክርና መግባባትን የራሳቸውን ሥልጣን ማጠናከሪያና የዓለምአቀፉን ማኅበረሰብ ማደናገሪያ አድርገው ሲጠቀሙበት ቆይተዋል። ብልጽግና ዛሬም የተለመደውን የኢህአዴግ ሥልታዊ ማደናገሪያ እንደገና ለመድገም እየሞከረች ነው። ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን በመጣ ማግሥት "የሰላምና ዴሞክራሲ ኮንፍረንስ" ብሎ በሰየመው ጉባዔ ላይ በዋናነት የራሱን ደጋፊዎችና አጃቢዎች ሰብስቦ

የሚፈልገውን ሁሉ በህገ መንግሥት ስም አጸድቆ ሥልጣኑን ያደላደለበት መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ኮንፍረንሱ አሳታፊ ከመሆን ይልቅ አግላይ ሆኖ በፖለቲካ ተንኮል የተተበተበና በድርጅታዊ አሠራር የተጠረነፈ ስለነበር እንኳንስ አገራዊ መግባባትን ሊያመጣ ቀርቶ ይበልጥ ከፋፋይ፣ ይበልጥ ጎጂ፣ የሆነ ሥርዓትና እነዚህንም አስፈጻሚ የሆኑ ተቋማትን በሕዝባችን ላይ የጫነ እንደነበር የምንገኝበት ዕውነታ አሳይቶናል።

የብልጽግናን ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላም የተቋቋመው የሰላምና እርቅ ኮሚሽንም አንድም ባለድርሻ አካላትን ሳያማክር በብልጽግና ብቸኛ ውሳኔ ላይ የተመሠረተ፣ አባሎቹም በብልጽግና ብቻ የተመረጡ፣ አንዳንዶቹም ህወሓት መሩ የኢህአዴግ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ የፖለቲካ ባልሥልጣኖች የነበሩ፣ አካታችነትና ግልጽነት የጎደለው ስለነበረ ጥቂት የኮሚሽኑ አባላት ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ጥረት ቢያደርጉም ከሦስት ዓመታት በኋላ ምን እንደሠራ እንኳን ለሕዝብ ሪፖርት ሳያቀርብ ባቋቋመው ብልጽግና ውሳኔ ኅልውናው ያከተመ መሆኑ የሚታወቅ ነው።

የሀገራችን ቀውስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰበ መምጣቱን በመገንዘብ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበረሰቡ አባላት፣ በሀገር ችግር ስጋት የገባቸው ዜጎች፣ ምሁራን....ወዘተ ያለፉትን የከሸፉ ሙከራዎች አሻሽሎ፣ አሳታፊና አካታች በሆነ መልክ አገራዊ መግባባት በአስቸኳይ እንዲካሄድ ደጋግመው አሳስበዋል። አሁን በሥራ ላይ ያለው የምክክር ኮሚሽን ደግሞ ከትላንትና ከትላንት ወዲያው ስህተት ትምህርት ባልወሰደ ሁኔታ ሲዋቀር ገና ከጅምሩ በጥርጣሬ እንዲታይ ሆኗል። በዚህ አኳያ የሚከተሉትን ነጥቦች ማንሳት ይገባል።

- የኮሚሽኑ የአመሠራረት ሂደት የተቃዋሚውን ግብዓት በተግባር ያካተተ አለመሆኑ፣
- ለብሄራዊ ምክክር ኮሚሽኑ አባልነት ተጠቆሙ የተባሉት 620 ተወዳዳሪዎች እነማን እንደነበሩ ከመጀመሪያው በግልጽና በይፋ አለመታወቁ፣
- ከ620ዎቹ መካከል ለሕዝብ ይፋ የተደረጉት 47 ዕጩዎች ውስጥ የውጭ ዜግነት ያላቸው፣ የኢህአዴግ አባላት የነበሩ ዲፕሎማቶች፣ የክልል መሪዎች...ወዘተ መካተታቸው፣



ስልክ / Phone : +251 944 223 216 ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com

- ከተሾሙት 11 ኮሚሽነሮች ውስጥ በ43ቱ የስም ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ ሦስት ግለሰቦች ድንገት መጨመራቸው በተመራጭ ኮሚሽነሮች ገለልተኛነትና በሂደቱ ተዓማኒነት ላይ ጥላ ያጠላበት በመሆኑ፣

- የኮሚሽኑን አካሄድ በተመለከተ ሂደቱ ከታች ወደላይ መሆኑ ጥሩ ሆኖ ሳለ የተሳታፊዎች አመላመል ግን የገዥውን ፓርቲ የበላይነት እንዲኖረው የተመቻቸ መሆኑ፣ ለምሳሌም በየቦታው የተደረጁ ወጣቶች፣ ሴቶች...ወዘተ የተደራጁት በገዥው ፓርቲ እንደሆነ እየታወቀ እነዚህ ክፍሎች በየደረጃው ከሁሉም ብልጫ ያላቸው ተሳታፊዎችን በማቅረብ በሂደቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በውጤቱም ላይ ወደ አንድ ጎን ያዘነበለ ከፍተኛ ተፅእኖ ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ፣

- ይህ እውነታ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገባና በጊዜ ማስተካከያ መንገድ ተግባራዊ እንዲደረግ ተደጋግሞ ቢነገርም እስካሁን ተግባራዊ አለመሆኑ፣

- በቅርቡ እንደታየው ደግሞ ገዢው ፓርቲ በሀገራዊ ምክክርና መግባባት ይፈታሉ ተብለው ይታሰቡ የነበሩ አከራካሪ ጉዳዮችን ውሳኔዎች እየሰጠባቸው መሆኑ፣ ለምሳሌ የመንግሥት የሥራ ቋንቋን በተመለከተ፣ የአዲስ አበባ ክልላዊ አስተዳደርን ጉዳይ፣ አዳዲስ ክልሎች የመፍጠር ጉዳይ፣ የሽግግር ፍትኅ ጉዳይ...ወዘተ እንዲሁም ራያ፣ ወልቃይትና ጠገዴን በተመለከተ እየወሰዳቸው የሚገኙት ውሳኔዎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ዋና ዋና ጉዳዮች ሲሆኑ ይህ አሠራር ገዥው ፓርቲ በኮሚሽኑ አማካይነት ወደ መግባባት ሊደረስባቸው ይችላል የሚባሉትን ጉዳዮች ቀድሞ እየወሰነባቸው መታየቱ በኮሚሽኑ ሥራ ውስጥ ጣልቃ እየገባ መሆኑን የሚያሳዩ በመሆኑ፣

- የኮሚሽኑ ተጠሪነት በብልጽግና ቁጥጥር ሥር ለሚገኘው ፓርላማ በመሆኑ ኮሚሽኑ የተቻለውን ያህል ጥረት ቢያደርግም በመጨረሻ ገዥው ብልጽግና ከሚፈልገው ውጭ ተግባራዊ የሚሆን ነገር አይኖርም የሚለውን ከፍተኛ ስጋት መደቀኑ የኮሚሽኑን ውጤታማነት ከፍተኛ ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል።

ከዚህ በተጨማሪ፡-

- ሀገራዊ ምክክርና መግባባት የሀገራችንን የቆዩም ሆኑ የአሁናዊ ችግሮች ለመፍታት



ስልክ / Phone : +251 944 223 216 ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com

የሀገራችን አሁናዊ ሁኔታ ኮሚሽኑ ሲመሠረት ከነበረው ሁኔታ ጋር እጅግ ይለያያል።

- ሀገራችን ዛሬ ያለችበት የፖለቲካ አውድ የራዕይ ግጭት ያለበት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች የተለያዩ ማኅበረሰቦችና ድርጅቶች የትጥቅ ትግል ውስጥ ገብተው የሚገኙበት ሁኔታ ውስጥ ነው ያለችው። በኦሮሚያ ቢያንስ ስድስት ዓመት፣ በአማራ ክልል አንድ ዓመት፣በቤኔሻንጉል፣በጋምቤላ ወዘተ የሚታይ እውነታ ይኸው ነው። መንግሥት የፖለቲክ ጥያቄዎችን በኃይል ለመፍታት ወይም ለማዳፈን የሚወስደው እርምጃ ችግሮች የበለጠ እንዲወሳሰቡና እንዲስፋፉ እያደረገ ነው። ሀገሪቱ በጦርነት እየደቀቀችና ህዝቡም የከፍተኛ የህይወት፣ የአካል ጉዳት፣ የመፈናቀል፣ የአገልግሎቶች እጦት ጉዳቶች እየደረሱበት ነው።
- ከዚህ በተጨማሪም ያለፉትን ስድስት የብልጽግና አገዛዝ ዓመታት ሲመረመር የፖለቲካ ምህዳሩ እጅግ የጠበበበት፣ የመናገር፣ የመጻፍ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ...ወዘተ መሠረታዊ መብቶች የተጣሱበት፣ ሕገወጥ እስራትና የሰዎች መሰወር የበረከተበት፣ በማንነት ላይ ያተኮረ ጥቃት የተስፋፋበት፣ በአማራና በኦሮሚያ ክልል ሰፊ ፖለቲካ ጋር የተያያዥ እስራት የበረከተበት ሁኔታ ይታያል።

ስለሆነም አገራችንን ለዘመናት ከገባችበት የጦርነት አዙሪት ውስጥ ለመውጣት:-

1. የሀገራችንን ውስብስብ ችግሮች በሀገራዊ ምክክር ለመፍታት ሁሉን ያካተተ ሂደትን እውን ለማድረግ ከሁሉም በፊት ጦርነት ቆሞ ከገዥው ፓርቲ ጋር

   በመሣሪያ ፍልሚያ ውስጥ የሚገኙ ኃይሎች በዚህ ሂደት ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡
2. መሣሪያ አንስተው በሚፋለሙ ኃይሎችና በገዥው ፓርቲ መሀል መተማመን ሊፈጥሩ የሚችሉ ርምጃዎችን ወስዶ የፖለቲካ ድርድር በማካሄድ የመሣሪያ ትግል ለማድረግ ያበቋቸውን ችግሮች በመዳሰስ ያነሷቸውን ጥያቄዎች መፍታት ይገባል።
3. በሁሉም ባለድርሻዎች ተሳትፎ የብሄራዊ ምክክር ሂደቱ ሊመረመርና የሚታዩት ህጸጾች ታርመው በአዲስ ሂደት ወደተፈለገው ሀገራዊ መግባባትና የፖለቲካ ሽግግር ሊያስኬድ የሚያችል ሁኔታ ላይ ግልጽ መስማማት ላይ መድረስ ያስፈልጋል።
4. መሠረታዊ የሆነውን የፖለቲካና ሰብዓዊ መብቶችንም በማክበር የፖለቲካ ድባቡ ለሀገራዊ ምክክር አስቻይ እንዲሆን ማድረግም እጅግ አጣዳፊ ተግባር ነው። መሠረታዊ ነፃነቶች ሊከበሩ ይገባል። በተለያዩ ምክንያንያቶች የታሰሩ የፖለቲካ



ስልክ / Phone : +251 944 223 216 ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com

ድርጅት አባላት፣የኢሕአፓን ሊቀመንበር ረዳት ፕሮፌሰር ዝናቡ አበራን ጭምሮ፣ ጋዜጠኞች፣ ማኅበራዊ አንቂዎች፣ በዘር ፍረጃ የታሠሩት ጭምር.....ወዘተ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ሊፈቱና ወደ ፖለቲካ መድረኩም እንዲመለሱ ማድረግ ይገባል።

5. አስቻይ ሁኔታዎችን ለመፍጠርም በሀገራችን የተለያዩ ክፍሎች የታወጀው አእቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነሳና ሕዝባችን የተረጋጋ ኑሮውን ሊመራ የሚችልበት ሁኔታ እውን ማድረግ ያስፈልጋል።

ኢሕአፓ ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በማጤን የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከምሥረታው ጀምሮ ችግር የነበረበት በመሆኑ፣ የኮሚሽኑን የሥራ ውጤትም የሚቀርበው ለገለልተኛ አካል ሳይሆን በብልጽግና አባላት ለተሞላው የተወካዮች ምክር ቤት በመሆኑ፣ ምክር ቤቱ ከብልጽግና ፓርቲ ጥቅም አኳያ በመመርመር የኮሚሽኑን የሥራ ውጤት ሊቀበለውም ሆነ ውድቅ ሊያደርገው እንደሚችል በማመን፣ ኮሚሽኑ በተሻለ መልክ ተዋቅሮ ገለልተኛነቱም አስተማማኝ እስካልሆነ ድረስ፣ ምንም እንኳን የኮሚሽኑ አባላት በቅንነት ሥራቸውን ሊያከናውኑ ይችላሉ የሚል ዕምነት ቢኖረንም፣ አሁን ባለው አወቃቀር አካሄድ፣ የፖለቲካ አውድ፣ ... የሀገራችንን መሠረታዊ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ ድምዳሜ ላይ ሊደረስ ይችላል የሚል ዕምነት የለውም። በተጨማሪ ኮሚሽኑ ሲመሠረት ከነበረው እውነታ ባሻገር የተፈጠሩ ግጭቶችን ለሀገራችን ቀውስም ወሳኝ ቦታ ያላቸው ሁኔታዎችን ለማካታት የሚያስችል ተልዕኮም ይሁን ህጋዊ ማዕቀፍ አለመኖሩ አሁን እየተካሄደ ባለበት መልኩ የኮሚሽኑ የሥራ ውጤት በአገራችን ውስጥ ዘላቂ ሰላምን ያመጣል ብሎ ኢሕአፓ አያምንም፡፡ ስለሆነም ኢሕአፓ ከዚህ ሂደት ውስጥ ከዛሬ ከግንቦት 26 ቀን 2016 ዓ. ም ጀምሮ ከላይ በቅደመ ሁኔታ ያስቀመጥናቸው እስከሚሟሉ ድረስ እራሱን ያገለለ መሆኑን ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በታላቅ አክብሮት ይገልጻል፡፡

በምትኩም አስቻይ ሁኔታዎች ተሟልተው ትክክለኛ ሁሉን አሳታፊ ነፃ አገራዊ የመግባባት ሂደት እውን እንዲሆን፣ የሀገራችንም ውስብስብ ችግሮች የሁሉንም ዜጎችና ማኅበረሰብ ክፍሎች ብሶትና ፍላጎት ባገናዘበ መልክ መፍትሄ ለመፋለግ የሚያስችል ሂደትን እውን ለማድረግ እንዲቻል ከሌሎች ተመሳሳይ ራዕይ ካላቸው ባለድሻዎች ጋር በመመካከርና በመተባበር በቅንነንት ለመሥራት ኢሕአፓ ወደፊትም ጥረቱን የሚቀጥል መሆኑን ቃል ይገባል።



ስልክ / Phone : +251 944 223 216 ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com

በአገራችን ውስጥ የሚገኙ ሁሉም የፖለቲካ፣ የሲቪክ ድርጅቶችና ሌሎች ባለደርሻዎችም ለዚህ ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ጥረት ሁሉ እንዲያደርጉ ኢሕአፓ ጥሪውን ያቀርባል።

ገዥው ብልጽግናም የድርጅታችንን ጥሪ በቅን መንፈስ ተመልክቶ ለአስቸኳይና ለሁሉን አቀፍ ድርድር ራሱን እንዲያዘጋጅ፣ ሀገራችን ከአውዳሚ ጦርነቶች ወጥታ ህዝቡም የሠላም ዐየር የሚተነፍስበት ሁኔታ እንዲፈጠርና እንዲሁም በምንም መልኩም ለሠላማዊ ፖሊቲካዊ መፍትሄዎች ፍለጋ የሚደረጉ ጥረቶችን ብልጽግና እንዳያደናቅፍ ኢሕአፓ ከወዲሁ ጥሪውን ያቀርባል።

ኢትዮጵያ አንድነትዋ ተከብሮ ለዘለዓለም ትኑር!
ጦርነቶች ቆመው ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍን እንሥራ!!
የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ
ግንቦት 26 ቀን 2016 ዓ. ም
አዲስ አበባ



ስልክ / Phone : +251 944 223 216 ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com